February 19, 2018

# በማሕበራዊ ሚዲያዎች የሚወጡ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ጎንደር ከቤት ያለመውጣት አድማ ላይ ነች ተባለ ።

በማሕበራዊ ድረገፅ አንድ ጦማሪ ይህን ፅፏል ። አሳረኛው ጎንደር አድማ ላይ ነው። የታክሲና የባጃጅ አገልግሎትን ጨምሮ ትራንስፖርት ሙሉ ለሙሉ ተቋርጧል። የፋሽስት ወያኔ ሰላዮችና ዘራፊዎች ከሆኑ የከተማው ትልልቅ ሆቴሎች በስተቀር ሁሉም ነገር ዝግ ነው። በሌላ በኩል ብአዴን የሚባለው የወያኔ ነውረኛ ድርጅት አውጫጭኙን በኤርትራዊው በረከት ሰምዖን መሪነት በባህር ዳር ከተማ እያገባደደ ይገኛል።

የኤርትራዊውን የበረከት ሰምዖንን የስራ መልቀቂያ አልቀበልም ብሎ ወደ ምድቡ እንዲመለስ ያደረገውና የግዑዙን የኃይለ ማርያም ደሳለኝን የስራ መልቀቂያ ግን በደቂቃዎች ፍጥነት የተቀበለው ሕወሓት የባሕር ዳሩን ጉባኤ በበከረት ሰምዖን የበላይነት ለመደምደም ጫፍ የደረሰ ይመስላል። ሕዝባዊ ተጋድሎው ግን ከጎንደር አልፎ ወደ ወሎ በመሻገር፤ ጎጃምን አሳብሮ ወደ ወለጋ፣ ሐረር፣ ሸዋን በማለፍ ባጠቃላይ ካገራችን ፋሽስት ወያኔ እስኪነቀል ድረስ ይቀጥላል!

